# ስለ COVID-19 በተደጋጋሚ የሚየቁ ጥያቄዎች እና የሜሪላድ ስራ አጥነት መድን ጥቅም አስተዳደር - የስራ አጥነት መድን

*(ይህ ዶክመንት የተተረጎመው በማርች 27 2020 ነው። ከዚህ ቀን በኋላ የታደሰ መረጃ ሊኖር ይችላል። ለዚህ ትርጉም አስፈላጊ እደሳዎች ሁሉም ጥረት ጊዜውን በጠበቁ መልኩ የሚደረግ ይሆናል።)*

## ጠቅላላ ጥያቄዎች

### 1. ስራ አሰሪዬ በጊዜያዊነት ስራዎችን በ COVID-19 ምክንያት የሚያቆም ከሆነ እና ይህ ደግሞ ወደ ስራ እንዳልመጣ የሚያደርገኝ ከሆነ፣ ለጥቅሞች ብቁ ነኝ?

COVID-19 በሚያመጣው በንግድ መዘጋት ምክንያት በጊዜያዊነት ከስራ እንዲወጡ የሚደረጉ ከሆነ፣ የስራ አጥነት መድን የስራ አጠነት መድን ይገባኛልን እንዲያመለክቱ ይመክርዎታል። ለስራ አጥነት መድን ጥቅም ይገባኛል ማመልከቻ ካስገቡ በኋላ፣ የስራ አጥነት መድን ክፍል የስራ አጥነት መድን ጥቅሞችን ለማግኘጥ ብቁ ነዎት ወይ የሚለውን የሚመረምር ይሆና። ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞችን እንላይን ማመልከትይችላሉ ወይም በስልክ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ከሰኞ እስከ አርብ፣ ባለው ጊዜ ውስጥ በ 410-949-0022 ስልክ (ባልቲሞር አካበቢ ካሉ እና ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም 800-827-4839 ላይ (ሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

### 2. በ COVID-19 ምክንያት ተለይቼ የምቀመጥ ከሆነ እና ወደ ስራ ለመመለስ የሚፈቀድልኝ ከዚህ ጊዜ በኋላ ከሆነ፣ ለጥቅሞች ብቁ እሆናለሁ?

በበሽታው ምክንያት ከስራቸው መቅረት ላለባቸው ሰዎች ምርጠ እና የመጀመሪያው ምርጫ ሊሆን የሚያስፈልገው ክፍያ ያለውን የእረፍት ጊዜያቸውን ጥቅም ላይ ማዋል ነው። የሜሪላንድ ጤነኞች ቤተሰቦች አዋጅ 15 እና ከዚያ በላይ ሰራተኞች ያላቸው አሰሪዎች ለአንዳንድ ሰራተኞች ክፍያ ያለውን የእረፍት ጊዜ እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል። 14 እና ከዚያ በታች የሆኑ ሰራተኞችን የሚቀጥሩ የሜሪላንድ አሰሪዎች ክፍያ የሌለውን የእረፍት ጊዜ እና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የእረፍት ጊዜ እንዲሰጡ ያስገድዳል። **ስለ ሜሪላንድ ጤና ሰራተኞች ቤተሰቦች አዋጅ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።**

“ስራ አጥነት” የስራ ሰአት እንዲሁም የክፍያ ቅነሳ ያጋጠማቸውን የሚያካትት ነው። ክፍያ ያለውን የህመም ወይም የቤተሰብ ጊዜ አረፍት የሚጠቀሙ ግን ደሞዛቸውን የሚያገኙ ሰዎች “ስራ አጥ” ተለብለው አይቆጠሩም የዚህም አላማው የስራ አጥነትን ጥቅም ለመሰብሰው አላማ ነው።

በአሁን ሰአት በጤና ባለሞያ ወይም በመንግስት መመሪያ መሰረት ተለይተው ተቀምጠው ከሆነ እና አሰሪዎ ደግሞ ተለይቶ መቀመጥ እስከሚያልቅ ድረስ ወደ ስራ እንዳይመለሱ አድርጎ ከሆነ እና በስልክ ለመስራት አማራጭን ያልሰጠዎ ከሆነ ክፍሉ የስራ አጥነት መድን ለስራ አጥነት መድን ማመልከቻ ያሰገቡ ዘንድ ይመክርዎታል። ይገባኛልዎን ካስቡ በኋላ የስራ አጥን መድን ክፍል የሰራ አጥነትን መድን ጥቅም ለማግኘት ብቁ ነዎት ወይ የሚለው ላይ ውሳኔ ያደረጋል። ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞችን እንላይን ማመልከትይችላሉ ወይም በስልክ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ከሰኞ እስከ አርብ ባለው ጊዜ ውስጥ በ 410-949-0022 ስልክ (ባልቲሞር አካበቢ ካሉ እና ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም 800-827-4839 ላይ (ሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

### 3. ምክንያታዊ በሆነ የ COVID-19 መያዝ ስጋት ምክንያት ስራዬን ለመልቀቅ የምወስን ከሆነ ወይም ለቤተሰብ አባል በ COVID-19 ምክንያት እንክብካቤ ለማድረግ ካለብኝ ለጥቅሞች ብቁ ነኝ?

ምንም አይነተ የኮሮና ቫይረስ COVID-19 ምልክት የሚያሳዩ ከሆነ እና የቅጥር ስራዎን ለማቆም የሚወስኑ ከሆነ የስራ አጥነት መድን ክፍል ለይገባኛል ማመልከቻ እንዲያስገቡ ይመክርዎታል በሜሪላንድ አዋጅ መሰረት ለጥሩ ምክንያት

እና/ወይም ትክክለኛ የሆነ ምክንያት ኖሮ በቂ የሆነ ስራን ለማቆም የሚሆን ምክንያት ያለ ከሆነ፣ እና የሚፈቀድ ከሆነ ብቁ እንደሆኑ ሊወሰንልዎ ይችላል፣ ክፍል 8-1001 ከሜሪላንድ የስራ አጥነት መድን ሽፋን ህግ ነው።

ይገባኛልዎን ካስቡ በኋላ የስራ አጥን መድን ክፍል የሰራ አጥነትን መድን ጥቅም ለማግኘት ብቁ ነዎት ወይ የሚለው ላይ ውሳኔ ያደረጋል። ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞችን ኦንላይን ማመልከትይችላሉ ወይም በስልክ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m፣ ከሰኞ እስከ አርብ ባለው ጊዜ ውስጥ በ 410-949-0022 ስልክ (ባልቲሞር አካበቢ ካሉ እና ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም 800-827-4839 ላይ (ሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

**4. በህመሜ ምክንያት የተወሰነ ሰአት እረፍት ለማድረግ የሚያስፈልገኝ ከሆነ፣ ነገር ግን በጤና ባለሞያ ወይም በመንግስት ህግ መሰረት ለስራ አጥነት ጥቅም ብቁ ልሆን እችላለሁኝ?**

በበሽታው ምክንያት ከስራቸው መቅረት ላለባቸው ሰዎች ምርጡ እና የመጀመሪያው ምርጫ ሊሆን የሚያስፈልገው ክፍያ ያለውን የእረፍት ጊዜያቸውን ጥቅም ላይ ማዋል ነው። የሜሪላንድ ጤነኞች ቤተሰቦች አዋጅ 15 እና ከዚያ በላይ ሰራተኞች ያላቸው አሰሪዎች ለአንዳንድ ሰራተኞች ክፍያ ያለውን የእረፍት ጊዜ እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል። 14 እና ከዚያ በታች የሆኑ ሰራተኞችን የሚቀጥሩ የሜሪላንድ አሰሪዎች ክፍያ የሌለውን የእረፍት ጊዜ እና ደህንነቱ አስተማማኝ የሆነ የእረፍት ጊዜ እንዲሰጡ ያስገድዳል። **ስለ ሜሪላንድ ጤና ሰራተኞች ቤተሰቦች አዋጅ ተጨማሪ መረጃ ያግኙ።**

በአሰሪው ለሚከፈል የእረፍት ጊዜ ብቁ ያልሆኑ እንደሆነ ወይም ይህ ጊዜዎ አብቅቶ ከሆነ፣ የስራ አጥነት መድን ክፍል የስራ አጥነት መድም ማመልከቻን ያስገቡ ዘንድ ይመክርዎታል። ከሰራዎ ለቀው ከሆነ እና እዚያው አሰሪዎ ጋር ወደፊት ለመመለስ እቅድ ያለዎ ከሆነ ብቁ እንደሆኑ ታይቶ ሊወሰንልዎ ያስፈልጋል።

ይገባኛልዎን ካስቡ በኋላ የስራ አጥን መድን ክፍል የሰራ አጥነትን መድን ጥቅም ለማግኘት ብቁ ነዎት ወይ የሚለው ላይ ውሳኔ ያደረጋል። ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞችን ኦንላይን ማመልከትይችላሉ ወይም በስልክ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ከሰኞ እስከ አርብ ባለው ጊዜ ውስጥ በ 410-949-0022 ስልክ (ባልቲሞር አካበቢ ካሉ እና ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም 800-827-4839 ላይ (ሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

**5. የምርት ሂደት በ COVID-19 ምክንት ተቋርጦ አሰሪው ሰራተኞችን ከስራ አባሮ ከሆነ፣ ሰራተኞቹ ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞች ብቁ ይሆናሉ?**

የሜሪላንድ ስራ አጥነት ጥቅሞች የእነርሱ ጥፋት ባልሆን ምክንያት ከሰራ ለተባረሩ ሰዎች በሙሉ የሚሰጥ ነው። በ COVID-19 ቀጥተኛ ምክንያትነት አሰሪው ሰራተኞችን የሚያባርር ከሆነ፣ የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ግለሰቦች ለስራ አጥነት ጥቅም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለስራ አጥነት መድን ይገባኛል ማመልከቻ ማስገባት ይችሉ። ለስራ አጥነት መድን ማመልከቻዎትን ኦንላይን ማስገባትይችላሉ  ወይም ከ ሰኞ እስከ አርብ፣ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ባለወ ጊዜ በ 410-949-0022 ቁጥር (በባልቲሞር ሜትሮ አካባቢ ወይም ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም በ 800-827-4839 ቁጥር (ሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

**6. በ COVID-19 ምክንያት አሰሪዬ የስራ ሰአቴን የሚቀንሰው ከሆነ፣ ለስራ አጥነት መድን ጥቅሞች ብቁ እሆናለሁ?**

አሰሪዎ የተለመደውን የስራ ሰአትዎን በ COVID-19 ምክንያት ቀንሶብዎ ከሆነ፣ ውስን ለሆነ ጥቅም ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ለስራ አጥነት መድን ማመልከቻዎትን ኦንላይን ማስገባትይችላሉ  ወይም ከ ሰኞ እስከ አርብ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ባለው ጊዜ በ 410-949-0022 ቁጥር (በባልቲሞር ሜትሮ አካባቢ ወይም ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም በ 800-827-4839 ቁጥር (ከሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

**7. በ COVID-19 ምክንያት አሰሪዬ ንግዱን ቢዘጋስ?**

በ COVID-19 ምክንያት አሰሪዎ ንግዱን ቢዘጋ፣ የስራ አጥነት መድን ክፍል የስራ አጥነት መድን ይገባኛል ብለው እንዲያመልክቱ ይመክርዎታል፣ ይህም የሚሆነው ያለእርሶ ጥፋት ከስራ ለቀው ስለሆነ ነው። ለስራ አጥነት መድን ማመልከቻዎትን ኦንላይን ማስገባትይችላሉ ወይም ከ ሰኞ እስከ አርብ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ባለው ጊዜ በ 410-949-0022 ቁጥር (በባልቲሞር ሜትሮ አካባቢ ወይም ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም በ 800-827-4839 ቁጥር (ከሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

### 8. ከቤት በርቀት የምሰራ ከሆነ የስራ አጥነት ጥቅሞችን መሰብሰብ እችላለሁ?

ከቤትዎ በርቀት ሆነው የተለመደውን የስራ ሰአትዎን የሚሰሩ ከሆነ፣ ስራ አጥ የሚለውን ትርጉም አያሟሉም። ነገር ግን፣ ከተለመደው ሰአትዎ ያነሰ የሚሰሩ ከሆነ ግን፣ ለስራ አጥነት መድን ይገባኛል ማመልከቻ ያስገቡ ዘንድ ይመከራሉ። ለስራ አጥነት መድን ማመልከቻዎትን ኦንላይን ማስገባትይችላሉ ወይም ከ ሰኞ እስከ አርብ ከ 7:30 a.m. - 3:30 p.m.፣ ባለው ጊዜ በ 410-949-0022 ቁጥር (በባልቲሞር ሜትሮ አካባቢ ወይም ከክልል ውጪ ከሆኑ) ወይም በ 800-827-4839 ቁጥር (ከሜሪላንድ ውስጥ ከሆኑ) ደውለው ማመልከት ይችላሉ።

### 9. ከደሞዜ ሌላ ከተጠቃሚዎች ጉርሻዎችን አገኛለሁ። የማገኘው ጉርሻ ምን ያክል ጥቅሞችን እንደማገኝ ለማስላት ጥቅም ላይ ይውላል?

አሰሪዎች አብዛኛውን ጊዜ የሰራተኞቻቸውን ደሞዝ በተከታታይ (በሩብ አመት አንዴ) ሪፖርት ያደርጋሉ። እነዚህ ደሞዞች ጉርሻዎችን ጨምሮ ማለት ነው፣ ምን ያክል ጥቅም ያገኛሉ የሚለውን ለመወሰን በሚደረገው ስሌት ውስጥ ይገባሉ። ጉርሻ የሚያገኝ ሰራተኛ ይገባኛል የሚል ማመልከቻ አስገብቶ የሚወሰንለትን የሳምንት ጥቅም በቂ አይደለም ብሎ የሚከራከር ከሆነ፣ በ 30 ቀናት ውስጥ ድጋሚ እይታ ለማግኘት ክለሳ ይደረግለለት ዘንድ መጠየቅ ይችላል። ከክለሳ ጥያቄው ጋር፣ ይገባኛል ጠያቂው፣ ሌሎች ደሞዞች እና ሪፖርት ያልተደረጉ ጉርሻዎችን ማስረጃዎች ማሳየት ይችላል።

### 10. በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ስራ መፈለግ ይጠበቅብኛል?

ክፍሉ እያንዳንዱ ይገባኛል ጠያቂ በሜሪላንድ የስራ አጥነት መድን ህግ ሰር ያለው ክፍል 8-903 የስራ መፈለግ መስፈርት ተሟልቶ የሆነ እንደሆነ ለማየት የይገባኛል ጠያቂውን ጥረት አሁን ካለው የስራ ቅጥር ገበያ አንጻር የሚያየው ይሆናል። በዚህ የስራ ቀጥር ሁኔታ ገበያው ሁኔታ ተለዋዋጭ በሆነበት ጊዜ ክፍሉ ይገባኛል ጠያቂዎች ስራዎችን እንፈልጉ ላይጠብቅባቸው ይችላል ነገር ግን፣ ሰራተኞች ሌሎች የዳግም ስራ ቅጥር ስራዎችን ይሰሩ ዘንድ ሊጠብቅ ይችላል፣ ይህም ሲቪ መፍጠር፣ ኦንላይክ ትምህርቶችን ማጠናቀቅ ወይም ሌሎች ፈቃድ ያላቸውን ኦንላይን ስራዎችን መስራት ሲሆኑ እነዚህም ይገባኛል ጠያቂው ወደፊት በተረጋጋው የስራ ቅጥር ገበያ ውስጥ ስራ መስራት ይችል ዘንድ ዝግጁ እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው።

ይገባኛል ጠያቂዎች ከስራ ያባረራቸው አሰሪያቸው ከ 10 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ እንደሚመለሱ ግልጽ አደርጎላቸው ከሆነ እነዚህ ይገባኛል ጠያቂዎች ስራ መፈለግ አያስፈልጋቸውም።

## አሰሪን የሚመለከቱ ጥያቄዎች

### 10. አንድ ሰራተኛ ወይም ከዚህ በፊት የነበረ ሰራተኛ ከኮሮና ቫይረስ ጋር ግንኙነት ባለው የንግድ መዘጋት ምክንያት የስራ አጥነት ጥቅሞችን አግኝቶ ከሆነ፣ የሰራተኛው የስራ አጥነት መድን ግብር ይጨምራል?

በ ኮሮና ቫይረስ COVID-19 ምክንያት ማንኛውም ቀጣሪ በ 2020 ላይ የግብር ጭማሪ አይታይበትም። የስራ አጥነት መድን ጥቅማ ጥቅሞች ለእየንዳንዱ ቀጧሪ እኩል የሚከፋፈለው በሰራተኛው መደበኛ የስራ ጊዜ ክፍያ መጠን ነው። የሚያዋጡ ቀጣሪዎች ለ COVID-19 ስለተከፈለው ጥቅማ ጥቅም ምክንያት በ 2021 ታክሳቸው ላይ ጭማሪ ሊያዩ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን የታክስ መጠን የሚሰላው በጁን 30 መጨረሻ ላለፉት ሶስት (3) አመታት ሰራተኛው እንዲከፍል በተደረገው ጥቅማ ጥቅም ነው። ስለዚህ፣ ከማርች እስከ ጁን በኮሮና ቫይረስ COVID-19ምክንያት የተከፈለ የትኛውም

ጥቅማ ጥቅም ለቀጣሪዎች የ 2021 ታክስ መጠን ለማስላት ጥቅም ላይ ከዋለው ከ 36 ወር ውስጥ አራት (4) ወሩን የሚያጠቃልል ነው።

ቀጣሪዎች በኮሮና ቫይረስ COVID-19 ለተከፈለ ጥቅማ ጥቅም ተቀናሽ እፎይታ የሚጠይቁ ከሆነ ይህን ለማድረግ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ይሰጣል። እየንዳንዱ ጉዳዮች ራሳቸውን ችለው ተቀናሾችን በተመለከተ የሚገመገሙ ሲሆን ህጉ እንደሚፈቅድ ይፈቀዳሉ።

ለተቀጣሪዎች ክፍያ ተመላሽ ማድረግ በፊት ለነበራቸው ሰራተኞች የተከፈለውን ጥቅማ ጥቅም ዶላር ለዶላር ያስከፍላል።